# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## የችቦና የደመራ መነሻ

የችቦና የደመራ መነሻ ታሪክ እንዴት እንደሆነ ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን ስንመረምርና አንዳንድ ሊቃውንትን አነጋግረን ያገኘናቸውን ጥቆማዎች ለአንባቢያን በመጠኑ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

ታሪኩም እንዲህ ነው የጥንቱ ኅብረተሰብ በተለይ ችቦን ይጠቀምበት የነበረው 1ኛ በዚያን ጊዜ እንደአሁኑ ዘመን ስልክ ፡ ቴሌግራም ፣ ወይም ሬድዮ ስላልነበረ በጊዜው የሚፈጸመው የነበረው የደስታና የድል የምሥራች በፍጥነት ለማዳረስከተራራላይ ሆነው በችቦ መልክ መብራት ያበራሉ በየተራራውም ወታደሮች ስለሚቀመጡ እነዚያ ደግሞ ሌሎቹን እየተከተሉ ያበራሉ በዚህ ዓይነት እየተቀባበሉ በመብራት ምልክት ደስታቸውን ለተቀሩት ክፍላተ ሀገራት እንዲዳረስ ያደርጉ ነበር

2ኛ በዚያን ጊዜ የነበሩት ኅብረተሰቦች የጣኦታቸውን በዓል የሚቀበሉት በዘንባባ ዝንጣፊና በችቦ እንደነበር ይናገራሉ ። ባጠቃላይ ግን ችቦ የሚበራው ለደስታ መግለጫ እንጂ ለሃዘን እንደማይበራ ይተረካል ።

የደመራው ታሪክ ደግሞ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ መጻሕፍት ሲያስረዱ ብዙ በሽተኞችንየፈወሰብዙሙታንንያስነሣ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል አይሁድ እንዲጠፋ አድርገውት ነበርና ንግሥት እሌኒ የጠፋውን የክርስቶስን መስቀል ለማግኘት ፍለጋዋን ከመጀመሯ በፊት በመጀመሪያ ምልክት ለማግኘት ስትል መስከረም 17 ቀን እርጥብ እንጨት አስቆርጣ ደመራ አስደምራ ካህናቱን ካጸለየች በኋላ በእሳት እንዲያያዝ አደረገች የደመራው/የዕጣኑ/ ጢስም መስቀሉ ወደተቀበረበት ቦታ ስላረፈ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቁፋሮው ፍለጋ እስከ መጋቢት 10 ቀን ቀጥሎ በመጋቢት 10 ቀን 327 ዓ.ም. የጠፋው መስቀል እንደተገኘ ያስረዳናል ።

ችቦ እንግዲህ የመስቀል ዕለት መብራት የተጀመረበት ዋናው ምክንያት ከላይ እንደገለጽነውና የቤተ ክርስቲያን ታሪክም እንደሚያስረዳው ንግሥት እሌኒ መስቀሉ በተገኘ ጊዜ ደስታዋን ለልጅዋ ለቆስጠንጢኖስ ለመግለጽ ጊዜው በሚፈቅደው የመገናኛ ዘዴ ሕዝቡ በየተራራው ችቦ እያበራ እንዲያስተላልፍ ስላደረገች ሳይዘገይ በችቦው ብርሃን አማካይነት የምሥራቹ ለልጅዋ ስለደረሰው በዚህ ምክንያት ተለመደ ይላል ።

ይኸው ታሪክ ሐተታውን በመቀጠል ቆስጠንጢኖስ የሠራውን መቅደስ በፐርሺያ ዛሬ ኢራን ተብሎ በሚጠራው አገር የነበረው ገዢ ንዋየ ቅድሳቱን ና ዕሌኒ አስቆፍራ ያስወጣችውን መስቀል ክርስቲያኖችንም ጭምር ማርኮ ከላይ ወደተጠቀሰው አገር ወስዶአቸ ነበር ። የቁስጥንጥንያ ንጉሥ614ዓ.ም. ው ነበር።የቁስጥንጥንያ ንጉሥ 614 ዓ.ም. ሕርቃል የፋርስ ንጉሥ የማረካቸውን ክርስቲያኖች ንዋየ ቅድሳትና መስቀሉንምጭምር እንዲመልስጠይቆት በ629 ዓ.ም. ጦርነቱ ቀርቶ በሙሉ ተስማምተው የማረከውን ዕቃ ፣ ሥዕል ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ለሕርቃል መለሰለት በዚሁ ጊዜ መስከረም 17 ቀን የዋዜማው ዕለት ማታ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ሕርቃል ዕቃውንና መስቀሉን ወደ ኢየሩሳሌም ይዞ ሲገባ በኢየሩሳሌም ከተማ ዳር የነበሩት ቃፊሮችና የከተማው ሕዝብ ችቦ እያበሩ ተቀበሉት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መስከረም 17 ቀን በየዓመቱ እንዲከበርና ችቦም እንዲያበራ ሆነ ይላል ። ይህም መልካም ተግባር በመሆኑ እየተለመደ ወደሀገራችን ደርሶ ቤተ ክርስቲያኖችንም ይህ መንፈሳዊ ቅርስና ከታሪክም ሲያያዝ የመጣ በመሆኑ በያመቱ መስከረም 17 ቀን በደማቅ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ።

በበዓሉ ዋዜማም ደመራ ተደምሮ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ጸሎት ይጸልያሉ ምህላ ያደርጋሉ በዚህም ዕለት ብዙ ሕዝብ በበዓሉ ሥፍራ ይገኛል በዚህን ጊዜ ደመራው ተባርኮ ከተቀጣጠለ በኋላ ሕዝቡ ችቦውን አቀጣጥሎ ደስታውን በሆታና በዕልልታ ያበሥራል ።

በዚህም ምሽት ሁሉም በየቤቱ በየደጁ ከዘመድና ከጐረቤት ጋር በመተባበር ችቦ ያበራል በአንዳንድ ጐሳም ለብዙ ጊዜ ተለያይተው የነበሩ ቤተሰቦች ለመስቀል በዓል ይገናኛሉ ። ይህም የመስቀል በዓል በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበረው በተለይ በጉራጌ፣በኦሮሞና በትግራይ ብሔረሰቦች ዘንድ ነው ይባላል።

እንግዲህ ደመራው የንግሥት እሌኒን ደመራ ምሳሌ የያዘ ሲሆን በሌላ መን

ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

